# ሁለቱ ኪዳናት

## ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ
## ወደ ዕብራውያን የጻፈውን መልእክት
## መሠረት በማድረግ

አዘጋጅ፡- መሪጌታ ኃየሉም በርሄ
አርታዒ፡- ዲያቆን ብርሃኑ አድማስ

በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን
በሰንበት ት/ቤቶች ማደራጃ መምሪያ
ማኅበረ ቅዱሳን

፳፻፪ ዓ.ም
አዲስ አበባ

©ማኅበረ ቅዱሳን

የመጀመሪያ እትም ፲፱፻፺፭ ዓ.ም
ሁለተኛ እትም ፳፻፪ ዓ.ም
ሦስተኛ እትም ፳፻፬ ዓ.ም

መብቱ በሕግ የተጠበቀ ነው
ALL RIGHTS RESERVED

ይህ መጽሐፍ
በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን
የሰንበት ት/ቤቶች ማደራጃ መምሪያ
በማኅበረ ቅዱሳን
ኤዲቶሪያል ቦርድ ታርሞ ተስተካክሉ የተፈቀደ ነው።

አድራሻ:-

በኢ/ኦ/ተ/ቤ/ክ
በሰ/ት/ቤቶች ማ/መምሪያ
ማኅበረ ቅዱሳን
ፖ.ሳ.ቁ 80078
አዲስ አበባ
ኢትዮጵያ

Email:- lemat@eotc-mkidusan.org
Website;-www.eotc-mkidusan.org

የኮምፒውተር ጽሑፍና ቅንብር
የኅትመትና ኤሌክትሮኒክ ሚዲያ ዋና ክፍል

# ምስጋና

ይህ መጽሐፍ በመሪጌታ ኃየሉም በርሄ ሲዘጋጅ በጥያቄና መልስ መልክ ነበር። መጠኑም ከዚህ ያነሰ ነበር። የማኅበሩ የኤዲቶርያል ቦርድ በሰጠው ማረሚያና ተጨማሪ ሃሳብ መሠረት መጽሐፉ ሰፋ ብሎ መዘጋጀት አስፈለገው።

ሁለተኛው ሥራ ብዙ ማገላበጥ፣ ማቀናበርና ነጥቦችን ለይቶ በየምዕራፉ ማውጣትን ይጠይቅ ነበር። ይህ ታላቅ ተልዕኮ የተሰጠው ዲያቆን ብርሃኑ አድማሴ ጊዜውን ሠውቶ አሁን በቀረበበት መልክ ስላቀናበረው ክፍላችን ምሥጋናውን ያቀርባል።

በሌላም በኩል ለዚህ መጽሐፍ ዝግጅት በዋና ማጣቀሻነት የተጠቀምንባቸውን መጻሕፍት በመላክ ከፍተኛ [illegible] ያደረጉልንን በአውሮፓና በአሜሪካ የሚገኙ የማኅበረ ቅዱሳን አባላትን [illegible] እግዚአብሔር ስም እናመሰግናለን።

የኅትመት ዝግጅት ማስተባበርያ ክፍል

በመተርጐም አይደለም:: በዚህ መንገድ «የቅዱስ ጳውሎስ መጽሐፍ ንባቡ ከነትርጓሜው» በሚል ርእስ በሊቃውንት ተተርጉሞ የተዘጋጀ መጽሐፍ ስላለ አዲስና ሌላ ተጨማሪ የትርጓሜ መጽሐፍ አያስፈልገም::

• የዚህ መጽሐፍ አጻጻፍ ግን ስለ አንድ ነገር የሚናገሩትንና በተለያዩ ምዕራፎች ላይ ያሉትን አሰባስቦ በአንዱ ምዕራፍ ሥር በመጨረስና በዚያ ዙሪያ ሰፋ ያለ ግንዛቤን በማቅረብ ነው:: ለአብነት ያህልም በዕብራውያን መልእክት ካሉት 13 ምዕራፎች ቢያንስ በስምንቱ ውስጥ ስለ ክህነት ተጽፏል:: በዚህ መጽሐፍ ግን «ክህነት» ራሱን የቻለ አንድ ምዕራፍ ሆኖ ምዕራፍ ሦስት ላይ ተጠናቅቋል:: ሌሎቹም በዚሁ መንገድ ተጽፈዋል:: ለየት ባለ መንገድ የተገለጸው ምዕራፍ አንድና በመጠኑ ምዕራፍ ሁለት ሲሆኑ በተለይ ምዕራፍ አንድ እያንዳንዱ ቁጥር ለብቻው ተተትኖ ተጽፎአል፤ ምክንያቱም የብዙ መናፍቃን መነሻና መሰናክያ ጥቅሶች በዚህ ሥር ስለሚገኙ ነው::

ይህ መጽሐፍ ለአንባብያን መጠነኛ ግንዛቤ ለማስጨበጥና ከመናፍቃን ቅሰጣ ምእመናን እንዲጠበቁና ወደፊትም «የአንድምታ ትርጓሜ» እያሉ ቢያወጡ በዚሁ መንገድ የቤተ ክርስቲያን መጻሕፍት አለመሆናቸውን ለማስገንዘብ የወጣ ነው:: ጥልቁን የቤተ ክርስቲያን ምሥጢር ደግሞ ከሊቃውንቱ በመጠየቅ እንደሚያዳብሩት እናምናለን::

እእምሮውን ለብዎውን ሰጥቶ ምሥጢሩን ይገልጥልን ጥበቡን ያሳድርብን ዘንድ ዕዝነ ልቡናችንን ይክፈትልን ዐይነ፣ ልቡናችንንም ያብራልን:: አሜን::

አርታዒው

ዲ.ብርሃኑ አድማስ



# ምዕራፍ 1

## በሥጋዌ የተናገረን የባሕርይ ልጁ ከሁሉ ይበልጣል::

«ከጥንት ጀምሮ እግዚአብሔር በብዙ ዓይነትና፣ በብዙ ጐዳና ለአባቶቻችን በነብያት ተናገር፣ ሁሉን ወራሽ ባደረገው ደግሞም ዘመናትን በፈጠረበት በልጁ በዚህ ዘመን መጨረሻ ተናገረን::»
ዕ.1–3

### 1.1. <u>እግዚአብሔር ከጥንት እስከ አሁን ተናገረን::</u>

<u>ጥንት:</u>– በዚህ መጽሐፍ ጥንት የተባለው ጌታችን ሰው ከመሆኑ በፊት የነበረው ጊዜ ነው:: በዚህ ጊዜ እግዚአብሔር በነብያት አድሮ በብዙ ዓይነትና በብዙ ጐዳና ተናግሮናል::

«እግዚአብሔር ከጥንት ጀምሮ በቅዱሳን ነብያቱ አፍ የተናገረው፣ ነገር ሁሉ እስከሚታደስበት ዘመን ድረስ ሰማይ ይቀበለው ዘንድ ይገባልና:: ሙሴም ለአባቶች ጌታ አምላክ እኔን እንዳስነሣኝ ነቢይን ከወንድሞቻችሁ ያስነሣላችኋል፤ በሚነግራችሁ ሁሉ እርሱን ስሙት:: ያንንም ነቢይ የማትሰማው ነፍስ ሁሉ ከሕዝብ ተለይታ ትጠፋለች አለ:: ሁለተኛም ከሳሙኤል ጀምሮ ከእርሱም በኋላ የተናገሩት ነብያት ሁሉ ደግሞ ስለዚህ ወራት ተናገሩ::» ይላል:: ሮሜ.3፥21–24:: በብዙ ዓይነትና በብዙ ጐዳና ተናገረን ሲልም ቃል በቃል፣ በምሳሌ፣ በትንቢት፣ በምሥጢራዊ ምሳሌያትና ምሥጢራውያት ትንቢቶች መናገሩን ነው::

ቃል በቃል ተናገረ የሚባለው እግዚአብሔርም ሙሴን «እንግዲህ....አለው» የሚለውን ዓይነት ነው:: እንደ ምሳሌም አሥሩ ቃላትን በመስጠት ተናግሮናል:: በምሥጢራዊ ምሳሌ የሚባለው

ብሂል ከሰው ሳይሆን ከእግዚአብሔር ነው:: በመንፈስ ቅዱስ ገላጭነት እንደ ተጻፉ በእርሱም አቅኝነት ሊተረጉሙ እንደሚገባ ተጽፎልና:: 2ኛጴጥ.1÷20:: ምክንያቱም የተጻፉት ለሰው ስለሆነ ምሥጢራዊውን ነገር ሁሉ ሰው በሚያውቀው ይገልጣሉ:: ይልቁንም ከሰው ስሜትና ኅሊና የመረዳት አቅም በላይ ስለሆኑት ነገሮች ሰው በሚያውቀው ምሳሌ መጻፋቸው የመጻሕፍት ልማድ ነው:: እግዚአብሔር አዳምን ጠርቶ «ወዴት ነህ?» እያለ መጠየቁ እንደ ሰው አሳብ እግዚአብሔር አዳም ያለበትን ያላወቀ ሊያስመስለው ይችላል፤ ይኸ ግን ከመነገር በላይ ያለውን የእግዚአብሔርን ፍቅር ለመግለጥ የተደረገ፣ ለሰውም ሊናገሩት የሚስማማ የአጻጻፍ ብሂል ነው:: ወደ ርእሳችን ከመመለሳችን በፊትም ለምሳሌ ያህል የአንድን ቃል መጽሐፍ ቅዱሳዊ ምሥጢር መመልከት የበለጠ ገልጽ ያደርግልናል::

<u>ቆመ</u> ምን ማለት ነው?

ሀ/ በእግር ጸንቶ በመሠረት ላይ መቆም:- በመሠረት ላይ በእግረ ሥጋ ወደ ላይ መቅናት /ቀጥ ማለት/ ነው:: መቆም የግድ መሠረትን ይጠይቃል፤ እስከ ጽንፍም /ጣሪያም/ መድረስ አይቻልም:: ይህ በእኛ ዘንድ የተለመደው ለሥጋዊ ለደማዊ ፍጥረት የታወቀው የተረዳው ትርጉም ነው:: «እርሱም ዳሰሰኝ ቀጥ አድርጉም አቆመኝ::» ዳን.8÷18 እንዲል::

ለ/ <u>መገለጥ</u>:- ከላይ ከለመድነው ውጭ ቆመ የሚለው ቃል የማይወሰኑ፣ ቀኝና ግራ የሌላቸውን፣ የፈጣሪንም ሆነ የረቂቃን ፍጡራንን ወይም የመናፍስትን መገለጥ ያመለክታል:: ለምሳሌ አብርሃም ቅድስት ሥላሴን በእንግድነት እንደ ተቀበለ በተጻፈበት የመጽሐፍ ክፍል ላይ «ዓይኑን አነሣና እነሆ ሦስት ሰዎች በፊቱ ቆመው አየ» /ዘፍ.18÷2/ ይላል፤ ተገለጡለት ለማለት ነው:: ምክንያቱም እግዚአብሔር መንፈስ ነው:: መሠረትና ጽንፍ የለበትም:: ነገር ግን ለአብርሃም በሰው አምሳል ማየት እንዲቻለው ፈቀዱለት፤ በወደዱትም መጠን ማስተዋል በሚችለው መንገድ ተገለጡለት ማለት ነው:: «እኔም ዳንኤል ራእዩን ባየሁ ጊዜ ማስተዋሉን ፈለግሁ፤ እነሆም የሰው ምስያ በፊቴ ቆሞ ነበር::» /ዳን.8 15/ ሲልም ተገለጠልኝ ማለቱ ነው:: «የጌታም መልአክ በዕጣኑ መሠዊያ ቀኝ ቆሞ ታየው::» ሉቃ.1÷11 የሚለውም ይህንኑ ያስረግጥልናል::



ሐ/ <u>ማገልገል</u>:- ከዚህም በላይ /ቆመ/ የሚለው ቃል /አማለደ/ የሚለውንም ትርጉም በቅዱሳት መጻሕፍት ይዞ እንመለከተዋለን:: «አብርሃም ግን በእግዚአብሔር ፊት ገና ቆሞ ነበር::» ዘፍ.18÷22 መባሉ እግዚአብሔር ውሱን አካል÷ ፊትና ጀርባ፣ ቀኝና ግራ አለው ለማለት አይደለም:: ይልቁንም የእግዚአብሔርን ገጸ ምሕረት እየተለማመነ፤ ማር! ይቅር በል! በማለት እያማለደ ነበር ለማለት ነው::

«እኔ በእግዚአብሔር ፊት የምቆመው ገብርኤል ነኝ» ሉቃ.1÷19 ሲልም የእግዚአብሔር ባለሟል ነኝ፤ ገጸ ምሕረቱን ደጅ ጠንቼ፤ ምሕረቱን ተቀብዬ ለደስታ ለብሥራት፣ ለምሕረት ለይቅርታ የምላክ የእግዚአብሔር ታማኙ ነኝ ማለቱ ነው::

«ዳግመኛም የጌትነቱን ብዛት ሊያሳይ ቢወድ÷ አስቀድሞ መርጦ በወደዳቸው ለይቅርታ የተዘጋጁ የይቅርታ መላእክትን ያመጣል::» /ሮሜ.9÷23/ ከተባለላቸው አንዱ እርሱ ነውና:: ይልቁንም ቅዱስ ዳዊት ስለ ሙሴ አማላጅነት በተናገረበት አንቀጽ «የተመረጠው ሙሴ በመቅሰፍት ጊዜ በፊቱ ባይቆም ኖሮ፣ ያጠፋቸው ዘንድ ተናገረ::» በማለት «መቆም» ማማለድ መሆኑን በማያሳብል መንገድ ገልጾታል:: መዝ.105÷23::

እንግዲህ ከላይ ያስቀመጥናቸውን ለግንዛቤ የሚረዱ ነገሮችንና ምሳሌውንም ከያዝን ወደ ኃይለ ቃላችን ትርጉም መመለስ

ቀኝህ ጠላቱን አደቀቀ::» ዘጸ.15÷6 ሲሉ ዘምረዋል::

እንግዲህ ቀኝ ከብዙ በጥቂቱ ይኸን የመሰለ ትርጉም ካለው ቅዱስ ጳውሎስ «በሰማያት በግርማው ቀኝ ተቀመጠ» ሲል የጻፈው ምን ለማለት ነው? ዳግመኛም ቁጥር 12 ላይ መዝ.109÷1 ጠቅሶ «ጠላቶችህን የእግርህ መረገጫ እስካደርግልህ ድረስ በቀኜ ተቀመጥ፤ ከቶ ለማን ብሏል?» ማለቱ ስለ ምንድን ነው?

ሀ/ <u>በሰማያት</u>:- ማለቱ መጀመርያውን በክብሩ በልዕልናው ማለቱ ነው:: ምክንያቱም እግዚአብሔር በሰማይ ያለ በምድር የሌለ ተብሎ ቦታ የሚወሰንበት አይደለምና:: «እናንተስ እንዲህ ጸልዩ:- በሰማያት የምትኖር አባታችን ሆይ...» /ማቴ.6÷9/ ማለቱ በልዑል መንበርህ በባሕርይ ልዕልናህ ጸንተህ የምትኖር በሉ ለማለት ነው::

ለ/ <u>ቀኝ</u>:- ሥልጣን፣ ዕሪና ማለት ነው:: ወልድ በተለየ አካሉ ሥጋ ቢለብስም በሥልጣኑ ከባሕርይ አባቱ ከአብ ከባሕርይ ሕይወቱ ከመንፈስ ቅዱስ ጋር ዕሩይ /ትክክል/ ነውና::

ሐ/ <u>ተቀመጠ</u>:- ይህን ማለቱ በመጽሐፍ «ዐረገ» ተብሎ ነበርና «የት ደረሰ?» ለሚለው ጥያቄ እርሱ የተሠወረ ረቅቆ የጠፋ ሳይሆን አሁንም ቅድመ ተዋሕዶ በነበረው የባሕርይ ጌትነት፣ ሥልጣንና ክብር አለ ለማለት ነው:: «ተቀመጠ» የሚለው ቃል አስፈላጊነትም ቀድሞ በሥላሴ ዘንድ ያልነበረ ግዙፍነት፣ በአካላዊ ቃል ፍጹም ተዋሕዶ ሥጋ ብእሲ /የሰው ሥጋ/ ለዚህ መብቃቱን፣ በተዋሕዶ እምላክ ለመሆን መታደሉን ለመናገር ነው::

መ/ <u>ጠላቶች</u>:- እንዲህ የተባሉት ደግሞ አይሁድ፣ መናፍቃን /ተጠራጣሪዎች/ እና አጋንንት ናቸው:: ጌታችን በወንጌል «ሰዎች ሲተኙ ግን ጠላት መጣና በስንዴው መካከል እንክርዳድ ዘርቶ ሄደ::» ማቴ.13÷25 እንዲል::

አጋንንት ጥንት ጀምረው በንጹሐን ኑሮ ላይ የጉስቁልና



ምክንያቶችና አዳምን ከእግዚአብሔር የለዩ እስካሁንም ይህንኑ የሚያደርጉ ናቸው::

አይሁድም በትንሣኤው ማግሥት «ሰው ነው ሞቷል፤ ደቀ መዛሙርቱ ሰረቁት እንጂ አልተነሣም» እያሉ ቀድሞ ከፈጸሙት በላይ የመጀመሪያ ግብራቸውን በማጽናት ለክርስትና ራሳቸውን ጠላት አድርገዋል:: መናፍቃንም ከንጹሑ የሐዋርያት ትምህርት ኋላ ለኋላ እየተከተሉ ኑፋቄንና በተአምራት ማታለልን ዘርተዋልና ጠላቶች ተብለዋል:: እነዚህ ቀድሞም በነብያት እንደ ነበሩ ማስታወስ ያስፈ ልጋል:: ለአብነትም ከይሁዳ ወደ ቤቴል በተላከው የእግዚአብሔር ነቢይ ላይ ሐሰትን ዘርቶ ሞትን ያመጣበትን ሐሰተኛ ነቢይ ማስታወስ ይቻላል:: 1ኛነገ.13÷1-ፍጻሜ::

ሠ/ <u>እግር</u>:- እንዲህ የተባሉት ደግሞ ሥልጣን፣ ምእመናንና መላእክት ናቸው:: መላእክትንና ምእመናንን «እግር» ያላቸው ስለ ምንድን ነው? ቢሉ እግር የአካል አንድ ብልት እንደ ሆነ ሁሉ መላእክትና ምእመናንም የክርስቶስ አካሉ የምትሆን የቤተ ክርስቲያን ብልቶች ስለሆኑ ነው:: አካልም አንድ እንደ ሆነ ብዙም ብልቶች እንዳሉበት ነገር ግን የአካል ብልቶች ሁሉ ብዙዎች ሳሉ አንድ አካል እንደሆኑ ክርስቶስ ደግሞ እንዲሁ ነው::» 1ኛቆሮ.12÷12 እንዲል:: እግርም በራሱ ሕይወት እንደሌለው የመላእክትም የምእመናንም ሕይወታቸው እግዚአብሔር ነው:: «እውነተኛ የወይን ግንድ እኔ ነኝ፤... እናንተም ቅርንጫፎች ናችሁ:: ያለ እኔ ምንም ልታደርጉ አትችሉምና» ዮሐ.15÷5 እንዲል:: ሰውን ተሸክሞ ወደ ልዩ ልዩ ቦታ የሚወስደው እግር እንደሆነው ሁሉ የሥላሴን መልእክት ይዘው የሚጓዙት መላእክትና ምእመናን ናቸውና::

ከላይ «ቀኝ»÷ ሥልጣን ነው እንዳልን.አሁንም «እግር» ማለት

ሥልጣን ማለት ነው ብለናል:: ምክንያቱም እግዚአብሔር በተለያየ መንገድ አንድን ነገር መግለጹ በቅዱሳት መጻሕፍትም ማጻፉ እኛ ነገሩን እንድንረዳው የሚያግዝበት መንገድ ስለሆነ ነው:: መንግሥተ ሰማያትን በብዙ ምሳሌ ማስረዳቱም የዚሁ አስረጂ ነው:: ሥልጣን «ቀኝ»÷ «እግር» ከመባሉም አልፎ «ቀንድ» እንደተባለም በቅዱሳት መጻሕፍት ሠፍሯል:: «እውነቴና ምሕረቴ ከእርሱ ጋር ነው፣ በስሜም ቀንዱ ከፍ ከፍ ይላል፡» መዝ.88÷24 ተብሎ በእግዚአብሔር ስም የቅዱስ ዳዊት ሥልጣኑ ከፍ ከፍ እንደሚል ተገልጿል:: ስለ ጌታችንም በመዝ.111÷9 ላይ «በተነ ለችግረኞችም ሰጠ፤ ጽድቁ ለዘላለም ዓለም ይኖራል፤ ቀንዱ /ሥልጣኑ/ በክብር ከፍ ከፍ ይላል::» ተብሎ ተጽፏልና::

በመሆኑም እግር ሥልጣን መባሉ በእግር እንዲረግጡበት እግዚአብሔርም የፈጠረውን ፍጥረት ሁሉ በእግሩ ርግጥ በእጁ ጭብጥ አድርጎ የሚገዛው በሥልጣኑ ነውና እግር ተባለ:: ቅዱሳን መላእክትና ምእመናንም የሥልጣኑ መገለጫዎች ናቸውና እግር ተባሉ:: ስለዚህ በትንቢት አስቀድሞ «ጠላቶችህን የእግርህ መረገጫ እስካደርግልህ ድረስ በቀኜ ተቀመጥ» ሲል:–

*ሀ/ ለጌታችን* :– በሞት ላይ የሠለጠነ ዲያብሎስን በሞትህ እስከምትገድልበት እስከ ዘመነ ሥጋዌ «በሞት ላይ ሥልጣን ያለውን በሞት እንዲሽር፣ ይኸውም ዲያብሎስ ነው::» ዕብ.2÷14 «የኋለኛው ጠላት የሚሻረው ሞት ነው፤ ሁሉን ከእግሩ በታች አስገዝቷልና:: ነገር ግን:– ሁሉ ተገዝቷል ሲል፣ ሁሉን ካስገዛለት /ከእግዚአብሔር/ በቀር መሆኑ ግልጥ ነው:: ሁሉ ከተገዛለት በኋላ ግን እግዚአብሔር ሁሉ በሁሉ ይሆን እንዴት ፈቀደለት?

– ለሞት ከራሱ በቀር ሁሉን ያስገዛለት እግዚአብሔር ነው:: ስለዚህም የሰው ሁሉ ጠላት ተባለ:: ለሞትም ሁሉ እንደተገዛለት



ቢቀር ከእግዚአብሔር ቀጥሎ ጌትነት ያለው በመሆን ይኖር ነበር:: ይህ እንዳይሆን ግን «ሁሉ በሁሉ» ይሆን ዘንድ ሁሉ የተገዛለት ሞት ሁሉን ያስገዛለት ወልደ እግዚአብሔር በፈቃዱ በሞተ ጊዜ ሁሉን ገዛ:: የእግዚአብሔር ሞት ግን ሞትን ራሱን ገደለውና ሥልጣኑን በሞት ሻረበት:: ሞትን የእግዚአብሔር ሞት ባይገድለው ኖሮ ሞት ነፍሳትን ሁሉ እያጋዘ አምላክ የሆነ በመሰለን ነበር:: ስለዚህ የእግዚአብሔር ሞት «ሞትን» የመግደል ሥልጣን ነበራትና ጠላት የተባለ በሞት ላይ የሠለጠነ ዲያብሎስ በእግዚአብሔር ሕይወት ሳይሆን በእግዚአብሔር ሞት ተገደለ:: የእግዚአብሔር ሞት ምን ያህል ልዩ ኃይል እንዳለው ማስተዋል ይገባል:: «ሁሉ በሁሉ ይሆን ዘንድ» ማለትም ሁሉን የገዛ ሞትን፤ ሁሉን ባስገዛለት በእግዚአብሔር ሞት ይገድለው ዘንድ ማለት ነው::

*ለ/ ያልተፈጸመች ሞተ ሥጋ ተፈጽማ ነፍስና ሥጋ ተዋሕደው* በአዲሲቱ መንግሥት ማስተዳደር እስከሚጀምርባት እስከ ዕለተ ምጽአት ድረስ:–

ቅዱሳት መጻሕፍት ኤልያስና ሄኖክን የመሰሉ ሰዎች ከሞት እንደ ተሠወሩ ይናገራሉ:: ዕብ.11÷5፣ 2ኛነገ.2÷7–14:: በሥጋ ልደትም አባትን ልጅ እየተካ አንዱ ሲሞት ሌላው እየመጣ እስከ ዕለተ ምጽአት ድረስ ሞተ ሥጋ እንደ ሠለጠነ ይኖራል:: ለወልደ እግዚአብሔር ግን ያልተገዛ ስለሆነ አይደለም፤ ሁሉም ይሞቱ ዘንድ ስላላቸው ነው እንጂ:: ሁሉንም አስገዝቶለታል ተብሎ ተጽፏልና:: «ሁሉን ከእርሱ በታች ባስገዛ ጊዜ ያልተገዛለት ምንም አልተወምና:: አሁን ግን ሁሉ እንደተገዛለት ገና አናይም::» /ዕብ. 2÷8/ በማለት ሞተ ሥጋን እያየን እንደሆነ ገልጿል::

በዕለተ ምጽአት ግን ሞተ ሥጋ ትፈጸማለች:: «ሞትና ሲኦልም በእሳት ባሕር ውስጥ ተጣሉ::» ራዕ.20÷14:: ቀዳማዊ ቃል

ነው:: 1ኛሳሙ.17÷34::

3. <u>ሀብተ መዊዕ</u>:- በዝናው ሳይቀር መርታት፣ ዜና ነገሩን ሲሰሙት መረበሽን ያመለክታል፣ የዳዊትም ዝናው ሲሰማ በዚህ በኩል መጣ ሲባል ጦሩ ሁሉ ይናድ ነበር:: 1ኛሳሙ.18÷30::
4. <u>ሀብተ በገና</u>:- በገና አዘጋጅቶ መደርደር፥ እግዚአብሔርን ማመስገን /1ኛሳሙ.18÷10/::
5. <u>ሀብተ ፈውስ</u>:- በሽተኛ የመፈወስ ሀብት ነው:: ቅዱስ ዳዊት በገና እየደረደረ ሳኦልን ከሚያሰቃየው ርኩስ መንፈስ ያሳርፈው ነበር:: /1ኛሳሙ.16÷23/
6. <u>ሀብተ ትንቢት</u>:- ትንቢት የመናገር ሀብት ነው:: ቅዱስ ዳዊት 150ውን ዳዊት በአሥር አርዕስት አድርጐ ትንቢት ተናግሯል::
7. <u>ሀብተ መንግሥት</u>:- የገዥነት ሀብት ነው:: ይኸውም የገደለውን ማስገደል፤ የቀማውን ወንበዴ ማስመለስና መቅጣት የመሰለ ነው:: ዳዊትም ንጉሠ እስራኤል ነበር::

ታዲያ በሰባት ሀብታት አንድ ሰው በኩረ ምእመናን ከሆነ ዳዊት ለምን አልሆነም:: ጌታችን ሃብታትን የሚቀበል ሳይሆን የሚሰጥ ነው:: እንኳን ሀብታትን ዘላለማዊ ሕይወትን የሚሰጥ ከአብና ከመንፈስ ቅዱስ ጋር በሥልጣን ሰፉይ ነው::

«አብ ሙታንን እንደሚያነሣ ሕይወትም እንደሚሰጣቸው፥ እንዲሁ ወልድ ደግሞ ለሚወዳቸው ሕይወትን ይሰጣቸዋል::» ዮሐ.5÷21 እንዲል:: ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስን ግን በኩረ ምእመናን ያሰኘው ይህ አይደለም:: እርሱ ክህነቱ የባሕርይው ነው ከማንም አልተቀበለውም:: ከእርሱ ሥጋዌ በፊት፣ በእርሱ የሥጋዌ ዘመን፣ ከእርሱም በኋላ ራሱን ካህን፣ ራሱን መሥዋዕት፣ ራሱን መሥዋዕት ተቀባይ አድርጐ ሰውን ከእግዚአብሔር ጋር



ያስታረቀ ሊያስታርቅም የሚችል ሌላ ካህን የለንም:: ለዘላለም ካህን ነህ የተባለው ክህነቱ የባሕርይው ስለሆነ ነው:: መዝ.109+4፣ ዕብ. 9+12፣ ሮሜ.5+10፣ 2ኛቆሮ.5+19::

የእርሱ መለኮታዊ ደም ከመፍሰሱ በፊትም ማንም ሰው ራሱን ከአዳም በደል /ከውርስ ኃጢአት/ ነጻ ማውጣት አልተቻለውም:: «ሁሉ ተሳስተዋል፥ በአንድነትም የማይጠቅሙ ሆነዋል::» /ሮሜ.3+12/፤ «ስለዚህ ምክንያት ኃጢአት በአንድ ሰው ወደ ዓለም ገባ፣ በኃጢአትም ሞት፤ እንደዚሁም ሁሉ ኃጢአትን ስላደረጉ ሞት ለሰው ሁሉ ደረሰ::» ሮሜ.5÷12 ተብሎ እንደ ተጻፈ:: ጌታችንም ይህን ኃጢአት አስወገደ:: «ኃጢአተኞችን ሊያድን ክርስቶስ ኢየሱስ ወደ ዓለም መጣ የሚለው ቃል የታመነና ሁሉ እንዲቀበሉት የተገባ ነው::» 1ኛጢሞ.1+15::

ስለዚህ ጌታችን በፈቃዱ ሰው ሆነ:: የዲያብሎስንም ሥራ አፈረሰ:: 1ኛዮሐ.3÷8:: ልጆች ተብለን የምንጠራበትን ሥልጣንና ፍቅር ሰጠን:: ዮሐ.1÷12፣ 1ኛዮሐ.3+1:: ለምእመናንንም የምግባር አብነት ለመሆን ጾሞ ሦስቱ አርእስተ ኃጣውእን ድል ነሣ:: ማቴ.4÷1–11:: እግር እስከ ማጠብም ራሱን ዝቅ አደረገ:: ዮሐ.13÷13::...ይህንና የመሰሏቸውን ሁሉ በማድረግ እንድንከተለው ጠራን:: ዮሐ.14÷6:: ቅዱስ ጳውሎስም እርሱን መምሰሉን ተረጐመው:: 1ኛቆሮ.11÷1:: እኒህን ሁሉ ግን በሥልጣኑ የሚያደርግ ከእርሱ በቀር ሌላ ባለመኖሩ በኩረ ምእመናን ተባለ::

1.8. <u>በደስታ ዘይት ቀባህ</u>:-

በእንተዝ ቀብዐከ እግዚአብሔር አምላክከ
ቅብዐ ትፍሥሕት እምእለ ከማከ
ስለዚህም እግዚአብሔር አምላክነትህ ቅባህ

«ክርስቶስ ከሙታን ተነሥቶ ወደፊት እንዳይሞት ሞትም ወደፊት እንዳይገዛው እናውቃለንና፡፡» ሮሜ.6÷9 እንዲል፡፡

ስለዚህ «አስነሣው» ተብሎ የተጻፈ ለአምላክነቱ እንደሆነ ሁሉ «ቀባህ» የተባለለትም «አምላክነቱን» ነው፡፡ ይኸም ማለት የተዋሐ ድከውን ሥጋ በራስህ አከበርህ፡፡ «እንቲአሁ ለቃል ኮነ ለሥጋ ወእን ቲአሁ ለሥጋ ኩነ ለቃል፡፡» የቃል የሆነው /መፍጠር፣መመለክ፣ መስገድ/ ፍጡር ለነበረ ለሥጋ ሆነ፡፡» እንዲል፡፡ አምላክነትህ ቀባህ ማለት ይኸ ነው፡፡ የሥጋ የሆነው /መራብ፣ መጠማት፣ መድከም፣ መሞት..../ ለቃል ሆነ፡፡ «ባለጠጋው በእርሱ ድህነት ባለጠጐች ትሆኑ ዘንድ ድህ ሆነ፡፡» የተባለውም ይህ ነው፡፡ እርሱን ድሀ ያደረገው የሚያሳንሰው፣ ባለጠጋ የሚያደርገው ቀብቶ የሚያከብረው የለም፡፡ እርሱ ሁሉን ማድረግ ይቻለዋልና፡፡

ራስን በራስ ማክበር ለእግዚአብሔር የተለመደ ነገር ነው፡፡ ፍጡርን ከመፍጠሩ በፊት ባሕርይውን ባሕርይው እንዳመስገነችው ባሕርይውን ባሕርይው እንዳከበረችው ፍጡሩን ከፈጠረ በኋላ ሰው በሆነ ጊዜ ባሕርይው /አምላክነቱ/ የተዋሕዶውን ሥጋ አከበረች እንጂ በሌላ አከበባሪ የከበረ፣ የተቀባም አይደለም፡፡ ቅዱስ ጳውሎስም የማንንም አከባሪነትና ባዕድ ክብርን እንዳልፈለገ ሲያጠ ይቅ በመዝ.101÷25–26 ቅዱስ ዳዊት የሰጠውን ምስክርነት በመጥቀስ አስረድቷል፡፡ «ጌታ ሆይ÷ አንተ ከጥንት ምድርን መሠ ረትህ፣ ሰማዮችም የእጅህ ሥራ ናቸው፡፡ እነርሱ ይጠፋሉ÷ አንተ ግን ትኖራለህ፣ ሁላቸው እንደ ልብስ ያረጃሉ÷ እንደ መጐናጸፊያም ትለውጣቸዋለህ÷ ይለወጡማል አንተ ግን ያው አንተ ነህ፣ ዓመቶችህም ከቶ አያልቁም» ብሏል፡፡



# ምዕራፍ ሁለት

## «ዓለምን ከፈጠረበት ጥበቡ ሰው ሆኖ ዓለምን ያዳነበት ጥበቡ ይበልጣል፡፡»

### 2.1. አብልጠን እንጠንቀቅ

«ስለዚህ ከሰማነው ነገር ምን አልባት እንዳንወሰድ÷ ለእርሱ አብልጠን ልንጠነቀቅ ያስፈልገናል፡፡ በመላእክት የተነገረው ቃል ጽኑ ከሆነ÷ መተላለፍና አለመታዘዝም ሁሉ የጽድቅን ብድራት ከተቀበለ÷ እኛስ እንዲህ ያለውን ታላቅ መዳን ቸል ብንለው÷ እንዴት እናመል ጣለን? ይህ በጌታ በመጀመሪያ የተነገረ ነበርና+ የሰሙትም ለእኛ አጸኑት÷እግዚአብሔርም እርሱ ራሱ እንደ ፈቀደ በምልክትና በድንቅ ነገር በልዩ ልዩ ተአምራትም÷ መንፈስ ቅዱስንም በማደል አብሮ መሰከረለት፡፡ዕብ2÷1–4፡፡

ቅዱስ ጳውሎስ በመጀመሪያው ምዕራፍ ላይ የጌታችንን ንግግር በንጽጽር አስቀምጦ ይልቁንም ደግሞ «የእግዚአብሔር ቃል መጣላቸው» የተባሉትን ነብያትንና የሚላላኩትን መላእክትን አን ሥቶ ከእነርሱ እንደሚበልጥ አስረድቷል፡፡ የእርሱን ከመላእክትም ከነብያትም መብለጥ ካመንን የእርሱ ንግግር ከሌሎቹ ይበልጣልና፣ ለእነዚያ ያልታዘዙት ከተቀጡ ለእርሱ የማንታዘዝማ የበለጠ ቅጣት ይጠብቀናልና እንጠንቀቅ ለማለት «ስለዚህ» ሲል ጀመረው፡፡

ሀ) ለነብያት ያልታዘዙ ተቀጥተዋል

ከሊቀ ነቢያት ሙሴ እንኳን ብንጀምር ብዙ ሰዎች እንዳጉረመረሙበትና እንደ ተቃወሙት ተጽፏል፤ በዘኁ.12÷1–15 እንደምንመለከተው አሮንና እኅቱ ማርያም ሙሴን ተናገሩት፡፡ እግዚ አብሔርም እነርሱን ገሠጻቸው፡፡ በተለይም ማርያምን በለምጽ

